# ገቢር ስድስት

**ምክንያት የሚቀርብበት ድምጽ**

አቡበከር - ቤተሰቦቼ ባደረግህላቸው አቀባበል በጣም ተደስተዋል፡፡ በእውነቱ በጣም አመሠግንሃለሁ::

አሮና - ይህ ትክክለኛ ነገር ነው ..ይህ የተለመደ ነገር ነው::

አቡበከር - አዎ! ሴት ልጅህን እንድትድርልኝ በማክበር እጠይቃለሁ

አሮና - እ ያ ችግር አይደለም የምመኘው ነገር ነው

አቡበከር - አዎ?

አሮና - ትክክል ቂ. ቂ. ቂ. . .

አሮና እና አቡበከር (ይስቃሉ)

አቡበከር- ለማንኛውም! እርሷን ለማስደሰት የሚቻለኝን ሁሉ አደርጋለሁ፡፡

አሮና - ደህና! በዚህ በኩል ምንም ጥርጥር የለኝም! ያንተ ባለቤት እንደማውቃት የአካባቢው ሴቶች ሁሉ የሚቀኑባት ነበረች::

አቡበከር - እርግጠኛም ነኝ ቤተሰቦቿ ምንም የገንዘብ ችግር የለባቸውም. . .

አሮና - እሺ! አቡበከር ከእርሷ ጋር እነጋገራለሁ::

አቡበከር - ደህና! እኔም ልሂድ! በቅርቡ እንደምንገናኝ ተስፋ አደርጋለሁ

- በነገራችን ላይ ሰዓቴ አስደናቂ ነገር ማሳየቷን አላስተዋልኩም ጃል

አሮና - እሺ! እህ

አቡበከር - እ... ይህን ልሰጥህ እሻለሁ

አሮና - አይ አይሆንም! (አሳፋሪ ሳቅ ይስቃል)

አቡበከር - (ይስቃል) አይሆንም! አጻምቀ! ይህ የእኔ ስጦታ ነው

አሮና - እርግጠኛ ነህ?

አቡበከር - አዎ እርግጥ ነው

አሮና - እንዴት እንደማመሠግንህ አላውቅም

አቡበከር - ምንም አይደለም!

አሮና - እሺ

አቡበከር - ከመጣበት ሥፍራ ብዙ አለ! ብዙ ጥሩ ነገሮችን እሠጥሃለሁ፡፡

አሮና - ኦ ልክ ነው! (በአስደናቂ ድምጽ ይስቃል) አስደናቂ ነው! (አስደሳች ጫጫታ) አዎ ልክ ነው!

አሮና - ፋቱ

ፋቱ - አቤት አባቱ

አሮና - መነጋገር ያስፈልገናል

ፋቱ - መልካም አባቱ

አሮና - (ይስቃል)

ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ - አሮና! አሮና! /ብሎ ይጣራል/

አሮና - ማነው እሱ ማነው?

(የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ድምጽ) - ላንተ የምነግርህ ነገር አለ

- እኔ የኤድስ ቫይረስ ነኝ ሴት ልጅህን ለዛ ሰው ከመስጠትህ በፊት በጥልቀት በረጅሙ አስብ! ብዙ የሴት ወይዘሮ ጓደኞች አሉት እኔንም ከቁም ነገር አልቆጠረኝም፡፡ ከምንም ነገር በላይ ስለ ልጅህ ጤንነት አስብ::

የአቡበከር ድምጽ - (በአሮና ጭንቅላት ውስጥ)

- ይህ ላንተ የሚሰጥ የእኔ ስጦታ ነው

የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ድምጽ (በአሮና ጭንቅላት ውስጥ)

- እኔ የኤድስ ቫይረስ ነኝ
- የአቡበከር ድምጽ (በአሮና ጭንቅላት ውስጥ)
- ብዙ ጥሩ ነገሮችን እሰጥሃለሁ

የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ድምጽ (በአሮና ጭንቅላት ውስጥ)

- ሴት ልጅህን ለዛ ሰው ከመስጠትህ በፊት በጥልቀትና በረጅሙ አስብ!

የአቡበከር ድምጽ (በአሮና ጭንቅላት ውስጥ)

- ምንም የገንዘብ ችግር የለም!

የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ድምጽ (በአሮና ጭንቅላት ውስጥ)

- ከሁሉም በላይ ስለ ልጅህ ጤንነት አስብ

የአቡበከር ድምጽ (በአሮና ጭንቅላት ውስጥ)

- ብዙ ጥሩ ነገሮችን እሰጥሃለሁ

የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ድምጽ (በአሮና ጭንቅላት ውስጥ)

- ብዙ የሴት ወይዘሮ ጓደኞች አሉት

የአቡበከር ድምጽ (በአሮና ጭንቅላት ውስጥ)

- ከዚህ ሌላም ብዙ ነገር አለ

የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ ድምጽ (በአሮና ጭንቅላት ውስጥ)

- አሮና! አሮና!

የአቡበከር ድምጽ (በአሮና ጭንቅላት ውስጥ)

- ብዙ ጥሩ ነገሮችን እሰጥሃለሁ! ብዙ ጥሩ ነገሮች! ጥሩ ነገሮች!

አሮና - (ይስቃል)

- ፊቶ ነይ እዚህ ተቀመጭ (ይስቃል)

- አቡበከርን አይተሽዋል ምን ታስቢያለሽ?

ፊቶ - አዎን አውቃለሁ ነገር ግን. . .

አሮና - እርሱ በጣም ሃብታምና ውብ ነው . . . ፊቶ

አሮና - ተጠንቀቁ ተጠንቀቁ ይኸው ነው ኧ

ዘበኛ - ጌታዬ

ፊቶ - ሄሎ ጤና ይስጥልኝ

ሸሮና - መልሰው

- እሺ ፊቶ የኔ ልጅ ነይ ግቢ

- አሮና - ተመልከች የባለቤትሽን ስጦታ ወንበሮቹ፣ ውብ መኖሪያ ቤቱ (ይስቃል)

- ስላየሁሽ ደስ ብሎኛል ተቀመጭ እስቲ! ና የልጄ ልጅ አሃ ለካ የእኔ ስመ ሞክሼ ነህ! (ከህፃኑ ጋር ይጫወታል) አዎ! ይሄ ነው አታልቅስ::

- ደህና! ምንድነው የምትነግሪኝ

ፊቶ - እርግጠኛ ለመሆን ጥሩ ዜና አይደለም

አሮና - ከባልሽ ጋር ሌላ ጠብ እንዳይሆን::

- ደህና! ችግሩ ምንድነው. . .

ፊቶ - ሆስፒታል የነበርኩበት ነው::

አሮና - ሆስፒታል? ለምን?

ፊቶ - ባለፈው ሳምንት የደም ምርመራ አድርጌ ነበር ኤች.አይ.ቨ. በደሜ ውስጥ ተገኝቷል::

አሮና - ኤች.አይ.ቨ. ፖዘቲቭ

- ልጁስ?

ፊቶ - እሱም ጭምር

አሮና - የፈጣሪ ያለህ! ልጁ ይቅር በይኝ! ይህ የእኔ ስህተት ነው ማድረግ አልነበረብኝም፡፡ እናንተን ለመረዳት ምን ማድረግ እችላለሁ. . .

ፊቶ - ታውቃለህ! ትንሽ ዘግይቷል. . .

አሮና - ፊቶ. . .

*******

## <u>ገቢር ሰባት</u>

የጋራ ተስፋ

ገቢሩ ሲጀመር የአኒ ልቅሶና መንሰቅሰቅ ይታያል

ማርያ (በመናደድ)

- እሺ! እሺ!

አኒ - ሌሎቹስ የታሉ?

ማርያ - ሳይወጡ አልቀሩም በዚህ ሰዓት እዚህ ሊኖሩ አይችሉም::

አኒ - (ትነፋረቃለች)

ማርያ - እሺ ንገሪኝ ምን እንደተፈጠረ!

አኒ - (በሃይል ትተነፍሳለች) እሺ! (ትነፋረቃለች) ይመስለኛል እሱ. . . (ትነፋረቃለች) አላውቅም! አዎ አውቃለሁ . . . ምን ላደርግ እንደምችል አላውቅም::

ማርያ - ምን ልታደርጊ እንደምትችይ ለምን አታውቂም?

አኒ - (ትነፋረቃለች) ምንም ላደርግ አልችልም ምንም መልስ ላገኝለት አልቻልኩም መልስ የለኝም (ትነፋረቃለች) ከዚህ በኋላ ምንም አልጠቅምም (ትነፋረቃለች) ከዚህ በኋላ ምንም አልጠቅምም (ታለቅሳለች) ምንም. . . (ትነፋረቃለች) ምንም (ታለቅሳለች)

አኒ - (ታለቅሳለች)

ማርያ - (በኃይል ትተነፍሳለች) አ! አኒ

አኒ - ሌሎችን ብቻ እንደሚገጥማቸው አስብ ነበር (ትነፋረቃለች፣ ታለቅሳለች)

- ማንም ሰው በራሴ ላይ ይመጣል ብሎ አይገምትም (ትነፋረቃለች)

ማርያ - አኒ!

- አኒ! አሁንም በጭንቀት ላይ ነሽ
- ነገር ግን ይህንን ለማለፍ ጥንካሬ አለሽ